**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሰበር ሰሚችሎት**

የሰ/መ/ቁ. 202681
ቀን ፡- ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ከበቡሽ ቡሎ
2. ወ/ሮ አስቴር አበበ
3. ወ/ሮ ወርቅነሽ አሰፋ
4. ወ/ሮ ወይንሸት ተክሌ
5. ወ/ሮ ቆንጂት ዘውዴ
} ቀረቡ

6. ወ/ራት አስናቁ ዓለሙ
7. ወ/ሮ እየሩሳሌም ገለቱ
8. ወ/ሮ አጸደ አረሩ
9. ወ/ሮ ተረፉ አረሩ
10. ወ/ሮ ጠጅነሽ ቴኒ
} ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ መንግሥቱ ባለህ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የስር ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ የንግድ ሥራ በልብስ ስፌት፣ በልብስ እጅ ሥራና ዝምዘማ የሥራ መደብ ተቀጥረን ስንሰራ ነሀሴ 28 ቀን 2011 ዓ/ም ከሕግ ውጭ በቃል ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ስለሆነ የአገልግሎት ክፍያ፣ ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት፣ ትርፍ ሰዓት የተሰራበት ክፍያ እንዲሁም ክፍያው ለዘገየበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቅጣት እንዲከፈላቸው እና የሥራ ልምድ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ በሕመም ምክንያት የተወሰኑ ወራትን አልነበርኩም፤ በዚህ ጊዜ በአደራ ሥራውን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ባለቤቴና ልጄ ናቸው፡፡ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት በመግጠሙ ጥሬ ዕቃ በገበያው ላይ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዚህ ለአመልካቾች ስራ ሳይሰሩ የሰኔ እና ሀምሌ ወር 2011 ዓ/ም ደመወዝ ተከፍሏል፡፡ እጥረቱ ሊቀረፍ ስላልቻለ ሠራተኞች ሳይሰሩ ከሚመላለሱ ተብሎ ብር 5,000.00 በመክፈል በመስከረም ወር እንዲመለሱ ገልጸን የተለያየን ቢሆንም በመስከረም ወር ስራ ለመጀመር መቅረብ ሲገባቸው ከሥራም ሳይሰናበቱ ክስ አቅርበዋል፡፡ አሁንም ወደሥራቸው ቢመለሱ ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 107631 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት ከቀረበው ማስረጃ በተሻለ የተረጋገጠው አመልካቾች በመስረም ወር 2012 ዓ/ም ወደሥራ ተመልሰው የነበሩ ቢሆንም ሥራ የለም ተብለው የተሰናበቱ መሆኑ ነው፡፡ በጥሬ ዕቃ ዕጥረት የተሰናበቱ ቢሆንም በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28 መሠረት የሚደረግ ስንብት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊከናወን የሚገባ ሲሆን ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ አመልካቾችን ከሥራ ማሰናበታቸው ከሕግ ውጭ የሥራ ውሉ እንደተቋረጠ ያረጋግጣል፡፡ ሥለሆነም የሥራ ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነው፡፡ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ ተጠሪ ለአመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል፤ የሥራ ልምድም ይሰጣቸው በማለት ሲወስን ትርፍ ሰዓት ሥራ መሰራቱ አልተረጋገጠም በማለት ዳኝነቱን ውደቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ የተቀበለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ አመልካቾች በክሳቸው የሥራ ውሉ ተቋረጠ በተባለበት ቀን ከሥራ የተሰናበቱ ስለመሆኑ ምስክሮቻቸው አላስረዱም፡፡ የተጠሪን ባለቤትና ልጅ እንደቀጣሪ በመቁጠር እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች መስከረም ወር ላይ እንዲመለሱ ተነግሯቸዋል በማለት መመስከራቸው፣ 2ኛ ምስክርም ከዚህ በኋላ እንዳትመጡ አላልኩም በማለት ያስረዳው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ማሰናበታቸውን አላስረዱም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በግራቀኙ ያልተነሳን መከራከሪያ በማንሳት በጥሬ ዕቃ ዕጥረት ነው የተሰናበቱት ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ማስጠንቀቂያ አለመስጠትም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ከሚያስከፍል በስተቀር ስንብቱን ሕገ-ወጥ አያደርገውም፡፡ ተጠሪ አምነው ያልከፈሉት ክፍያ ስለመኖሩ የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈል መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በሚል ካሣ፣ የሥራ ስንብት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ተጠሪ እንዲከፍሉ የተሠጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የሥራ ውላችን ከሕግ ውጭ መቋረጡ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ባለቤትና ልጅ ሥራውን በአደራ ያስረከቧቸው ስለመሆኑ ተጠሪም አምነዋል፡፡ ውሳኔው ሕግን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርሕን የተከተለ ስለመሆን አለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ የታዘዙ ሲሆን ያቀረቡት መልስ አመልካች ከሥራ መሰናበታቸውን

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አላስረዱም፡፡ ማስረጃው ተመዝኖ የተወሰነ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአመልካቾች የሥራ ውል የተቋረጠው በአሠሪው አነሳሽነት ወይስ በሠራተኛው አነሳሽነት? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ የንግድ ሥራ በልብስ ስፌት፣ በልብስ እጅ ሥራና ዝምዝማ የሥራ መደብ ተቀጥረን ስንሰራ ነሀሴ 28 ቀን 2011 ዓ/ም ከሕግ ውጭ በቃል ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ስለሆነ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው እና የሥራ ልምድ እንዲሰጣቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት በመግጠሙ ጥሬ ዕቃ በገበያው ላይ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዚህ ለአመልካቾች ስራ ሳይሰሩ የሰኔ እና ሀምሌ ወር 2011 ዓ/ም ደመወዝ ተከፍሏል፡፡ እጥረቱ ሊቀረፍ ስላልቻለ ሠራተኞች ሳይሰሩ ከሚመላለሱ ተብሎ ብር 5,000.00 በመክፈል በመስከረም ወር 2012 ዓ/ም እንዲመለሱ ገልጸን የተለያየን ቢሆንም በመስከረም ወር ስራ ለመጀመር መቅረብ ሲገባቸው ከሥራም ሳይሰናበቱ ክስ አቅርበዋል፡፡ አሁንም ወደሥራቸው ቢመለሱ ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡

በተያዘው ጉዳይ እያከራከረ ያለው የአመልካቾች የሥራ ውል በተጠሪ አነሳሽነት የተቋረጠ ነው ወይስ በአመልካቾች በራሳቸው ሥራውን በመተዋቸው የሚል ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ውላችን በተጠሪ የተቋረጠ ነው ያሉ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 259 እና 260 መሠረት የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ጠቅሶ የሚከራከር ወገን ፍሬ ነገሩ ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ስላለበት ውሉ በተጠሪ መቋረጡን ማስረዳ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶ አመልካቾች

በተጠሪ ስለመሰናበታቸው ተረጋግጧል በማለት የወሰነ ቢሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ማስረጃው በአግባቡ አልተመዘነም በሚል አመልካቾች በክሳቸው የሥራ ውሉ ተቋረጠ በተባለበት ቀን ከሥራ የተሰናበቱ ስለመሆኑ ምስክሮቻቸው አላስረዱም፡፡ የተጠሪን ባለቤትና ልጅ እንደቀጣሪ በመቁጠር እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች መስከረም ወር 2012 ዓ/ም ላይ እንዲመለሱ ተነግሯቸዋል በማለት መመስከራቸው፣ 2ኛ ምስክርም ከዚህ በኋላ እንዳትመጡ አላልኩም በማለት ያስረዳው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ማሰናበታቸው በሚገባ አላስረዱም ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና ሂደት የተፈጸመ የማስረጃ ሕግና ማስረጃ ምዘና መርሕ ጥሰት መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በተጠሪ የሥራ ውላቸው መቋረጡን ያላስረዱ በመሆኑ ካሣ፣ የሥራ ስንብት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ተጠሪ የሚከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 249944 ጥር 27 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም